ደብዳቤ

- መልእክትን በፅሁፍ ለማስተላለፍ ያገለግላል።
- ናፍቆትን ፣ ደስታን፣ ሀዘንን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን ፣ወዘተ በፅሁፍ ለማስተላለፍ ያገለግላል።
- በአጠቃላይ የሰዉን ልጅ ዉስጣዊ ስሜቱን በደብዳቤ ይገልፃል።

የደብዳቤ አይነቶች

1. የግል (የወዳጅ ዘመድ) ደብዳቤ
2. የመስርያ ቤት ደብዳቤ
3. የማመልከቻ ደብዳቤ

1. የግል(የወዳጅ ዘመድ) ደብዳቤ

ግለሰብ ለግለሰብ የሚፃፍ ነዉ።

ለምሳሌ፦ የፍቅር ደብዳቤ ፣ የወቀሳ ደብዳቤ፣ የሀዘን መግለጫ ደብዳቤ፣ የምስጋና ደብዳቤ፣ የደስታ መግለጫ ደብዳቤ ፣ የምስጋና ደብዳቤ እንዲሁም የግብር ጥሪ ደብዳቤ ይገኙበታል።

በተጨማሪም በዚህ የደብዳቤ አይነት ሰዎች ስለስራቸዉ፣ ስለቤተሰባቸዉና ስላሉበት አካባቢ ወዘተ መረጃዎችን ይለዋወጣሉ።

ለወዳጅ ዘመድ የሚጻፍ ደብዳቤ የሚከተለዉን ቅርፅ ይኖረዋል።

ራስጌ

_____ (1)ቀን

_____
_____ (2) የላኪ አድራሻ

_____
_____ (3) የተቀባይ አድራሻ

_____
_____
_____
_____ (4) የመግቢያ ሰላምታ

_____
_____
_____
_____
_____
_____.(5) ሐተታ

_____
_____

2. የመስሪያ ቤት ደብዳቤ

የበታች መስሪያ ቤቶች ለበላይ መስሪያ ቤቶች ወይም የበላይ መስሪያ ቤቶች ለበታች መስሪያ ቤቶች የሚፅፉት ደብዳቤ ነዉ።

- ✓ መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤት
- ✓ መስሪያ ቤት ለድርጅት

- ✓ ድርጅት ለድርጅት የሚፃፃት ደብዳቤ ነዉ።

3. የማመልከቻ ደብዳቤ
   - ➢ ግለሰብ ለመስሪያ ቤት
   - ➢ ግለሰብ ለድርጅት የሚፅፈዉ ደብዳቤ ነዉ።
   - ➢ ሰዎች ስራ ለመቀጠር ፣ አቤቱታ ለማቅረብ ወዘተበማመልከቻ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ።

የደብዳቤ ክፍሎች

1. መግቢያ ፡- የሰላምታ ልዉዉጥ የሚካሄድበት፣ ለሀተታዉ መንደርደሪያ ሀሳቦች የሚነሱበት
2. ሀተታ፡- ሊተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት በዝርዝር የሚቀርብበት
3. መደምደሚያ፡- ማጠቃለያ እንደመሆኑ መጠን ከላይ በሀተታዉ የተዘረዘረዉና የተተነተነዉ ሀሳብ ጠቅለል ብሎ የሚቀርብበት ክፍል ነዉ።

መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እዉነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።

_____1. በደብዳቤዉ ላይ ሊተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት በዝርዝር የሚቀርብበት የደብዳቤ ክፍል ሐተታ ይባላል።

_____2. ደብዳቤ መልዕክትን በፅሁፍ ለማስተላለፍ ያገለግላል።

_____3. የፍቅርና የደስታ መግለጫ ደብዳቤለመስሪያ ቤት ደብዳቤ ምሳሌ ይሆናሉ።

_____4. በወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ ሰዎች ስለራሳቸዉ ስለቤተሰባቸዉ ላሉበት አካባቢ መረጃን ይለዋወጣሉ።

_____5. የመስሪያ ቤት ደብዳቤ አንዱ የደብዳቤ ክፍል ነዉ።